# ኢትዮጵያ ዛሬ፡ ትናንትና ከነገ ወዲያ

ከዶ/ር ታዬ ወልደስማያት

ኢትዮጵያ እንደ አገር ከተመሰረተችበት ዘመን አንስቶ ትልቁ የሃገራችን የሶሻል ስቆቃና ጣረ ሞት የፓለቲካ ማህበራዊ ሕይወት ትልቁ የችግሮች መንስኤው የእኩልነት ጥያቄ ነው። በሁሉም አቅጣጫ በህብረተሰቡ የፓለቲካ ታሪክ ወስጥ ወጥሮ የያዘው የእኩልነት ፍላጎት ብቻ ነው።ዛሬም ነው ትናንትም ነበር ነገም ነው። ጥያቄውን

**መልስ ያለመስጠት መፈለግ ለውጥን ለማቆም መሞከር ተስፍ ቢስ ነው ። በቅርብ ያለውን የፓለቲካ አመራር እንዲህም የፓለቲካው ውዝልቅ ብዙዎች የስቨል ጦርነቶች፡ የተማሪዎችና የአስተማሪዎች እመጽ ፡ የሠራተኞች ኑሮውን ለማሻሻል ያደረገው የሥራ ማቆም አድማ የፍትህ ጥያቄዎች የህዝብ ንቃተ - ህሊና ከፍታ በአገሪቷዋ መላው ህብረተሰብ የፓለቲካው መዋቅር የፈጠረው ኢ-እኩልነት ሁኔታ ነው። ሃብት ማካበት ስልጣንና የሕዝቡን አመኔታ ማጣት ነው።ዋናውና ተቀዳሚው ችግር እኩልነት ፓለቲካው ማምጣት ያለ መቻሉ ነው። ስለዚህ ስርዓቱን የሕጋዊነት ውዝልቅ(legitimacy crisis) ገብቶአል።**

የዚህ ስርዓት ባለቤት ነን ብለው ዝም ብለው በማይሆን ክርክር ወደ ጎን አደርገው ወደ ዋናው ችግሮችን ማተር ይኖርባቸዋል። ዋናው መፈክር ሆኖ የፓለቲካውን ውይይት መደረክ አጣቦ ያለው። ይህ አቅጣጫ ያጣ የመንግሥት ስርዓት ዋና አደርጉው በሙብት ስበብ የያዘው ህዝብ መከፋፈልን ነው ። በአሁኑ ጊዜ በፓርላማው ውስጥ እየተካሄደ ያለው የሕዝብን ስሜት በብሔር ና በድንበር በሃይማኖትና በማንነት ጥያቄ በመከፈልላይ ነው። ህዝቡ እንደ አጋር በመሆን በጋራ በአንድነት የጋራ ጠላቶቹን እንደ በሽታ፡ዘረኝነትን ፡ ጽተኝነትን፡ ኢ-እኩልነትን፡ ድንቁርናን፡ አክራሪነትን አጥብቆ እንዳይዋጋ የተደረገ ሴራ ነው። አቶነሚ የሚባለው ንድፈ-ሃሳብ ጭቆናንና ብዝበዛን ሲፈታ አልታየም። በርግጥም የሚደረግ ነገር ካለ ዋና ዋና ችግሮች ላይ እንድናተኩር ማደረግ ሲሆን ለዚህ ሄደት መፍትሄው ደህነነትን ብዝበዛን ና ኢ-ፍትሃዊነት ታግሎ ማሸነፍ ብቻ ነው። በመጨረሻ የፓለቲካ ድርጅቶች።

ምንም ነገር ይሁን የፓለቲካ ለውጥ የህግ የበላይነት እንዲከበር ያድርጉ እንጅ ምንም ዓይነት የፓለቲካ ኃይልና አቅም አይታይባቸውም። በፍልስፍና ደረጃ እንካን የኒዎ ልብራልዝምን የኤኮኖሜክ ፐሊሲን መቃውም ማናቸውም አላስሙም ስለሆነም ከነዚህ ሃይሎችን እኩልነትና ነፃነት ያመጣሉ ብሎ ማስብ አይቻልም። ስለዚህም ሕዝብ ያለው አማራጭ መደራጅት ፡ መደራጅት ብቻ ነው።

ውዝልቅ የሚለው ቃል የመጣው ከሽማኔው ህብረተሰብ ነው። ድርና ማጉ እርስ በርስ ተጠላልፎ ውሉ ጠፍቶ ሲወሳስብ ድሩ ውዝልቅ ወስጥ ገብቶለታል ይላል።

የዚህ ጽሁፍ ሰፊ ትንታኔ በቅርቡ ይወጣል !